# መዋሸት የወያኔ ግፈኞች በተለይ የሚታወቁበት!

ወያኔ ወይም ሕወሓት ከተመሰረተበት ወቅት ጀምሮ እውሸትን እንደ አንድ የፕሮፓጋንዳው ትግል መሳሪያ አድርጎ በመጠቀም እስካሁኗ ደቂቃ ድረስ በእቅድ እየተጠቀመበት የመጣ ነፍሰ ገዳይ ድርጅት ነው።

1.የትግራይ ሕዝብና ሕወሓት አንድ ናቸው? ሕወሓትና የትግራይን ሕዝብ አንድ ነው ለማለት የሚደረገው ፕሮፕጋንዳ እውሸት ለመሆኑ „የአማራ ቡችላ" እያለ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩትንና የእሱን የዘር ፖለቲካ የማይከተሉትን ወያኔ ትግራይ ውስጥ ፈጅቷል።ሌሎችንም የኢዲዩ አባል ነህ በማለት ባዶ ሽድስተ በማስገባት፣ መሬት ውስጥ ሁለት ሜትር ወደታች ራሳቸውን በማስቆፈርና በኋላም ጉርጓዱ ውስጥ በመከተት፣ ቶሎ እንዳይሞቱ በተወሰነ ግዜ ደረቂ ቂጣ በሜንጦ ብረት እያቀመሷቸው ቀይ ምስጥ እየበላቸው ሲሞቱ አፈር እያለበሷቸው ናዚ ከሰራው በከፋ መንገድ ጨርሰዋቸዋል።በአንድ የትግራይ አካባቢ ወያኔ የፈጃቸው የትግራይ ተወላጅ መሬቱ ቢቆፈር የትግራይ ተወላጅ አጽም በገፍ የሚገኝበት ቦታ እንዳለ ነው።

የእነርሱን ዘረኛ ፖለቲካ የማይፈልጉትን የትግራይ ተወላጆች የተለያዩ ስም በመስጠት ከገዱሉ በኋላ ከብቶቻቸውን፣ መሬታቸውንና ሌሎች ንብረታችውን ወያኔ ትግራይ ውስጥ ወርሷል። የውጪ ሃይላት ደጋፊዎቻችውን ለማሳመን የተወሰኑ የቪዲዮ ካሜራ አንሺዎችን ውጪ አስልጥኖ ወደ ትግራይ በማስገባት፣ ለደርግ በገበያ ቀን ህወሓት ስብሰባ እንደሚያደርግ መረጃ አሾልኮ በመስጠት፣ ደርግ ሕዝቡን በገበያ ቀን በአውሮፕላን እንዲፈጅ አድርጓል።ይህንንም ከውጪ አሰልጥኖ ባዘጋጃቸው የቪዲዮ ካሜራ አንሺዎች አስነስቶ ወዲያውን በሱዳንና በምዕራቡ ዓለም እንዲሰራጭ አስደርጓል።

ይህ ሁሉ ግፍ ዛሬ የወያኔ መንግስት ሊደበቅበት የሚፈልገውን የትግራይ ህዝብ ላይ ያደረሰው ግድያ ነው።በዚህ ምክንያት ሕዝቡ ተማሮ ሕወሓትን እንዲቀላቀል ለማድረግ ነበር።ተሳክቶለታል። ሕዝቡ የነበረው አማራጭ ሕወሓትን መቀላቀል ወይም ከቻለ አገር ጥሎ መውጣት ነበር። ዛሬም ከዚህ የተለየ አይደለም።የትግራይ ተወላጅ የሆነ ለወያኔ መንግስት አሽከር ሆኖ ለጥ ጸጥ ብሎ የማይገዛ ከሆነ፣ የግፋቸው ሰለባ ይሆናል። ያለበለዚያም አገር ጥሎ መውጣት ነው።ስለዚህ „የትግራይ ሕዝብ ሕወሓት ነው።
ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ ነው።" የሚለው አባባል ከዚህ የመነጨ ነው። እውሸት አንድ ነው።የትግራይ ሕዝብ በሙሉ የወያኔ አባል አይደለም።በፍርሃት ዝምታን የመረጡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች አሉ።አንድ ለአምስት የሚለውም ብትንትኑ ይወጣል።ጭራሽም አምስት ለአንድ አድርገው ወደፊት ሊጠቀሙበት የሚችሉብትን እድል ይፈጥራል።

2.ሕወሓት ለኢትዮጵያ አደገኛ መሆኑን ሕወሓት ዘረኛና የትግራይ ትግሪኛን ለመመስረት የሚንቀሳቀስ ጸረ-ኢትዮጵያ የሆነ ድርጅት በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይቀበለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሬዲዮና በቴሌቪዥን በደርግ ግዜ ኢትዮጵያ ገብተው ያሳሰቡት አቶ ገብረ መድህን አርአያና አቶ አብርሃም ያየህ ናቸው።ሁለቱም ኢትዮጵያውያን የትግራይ ተወላጆች ናቸው።በዚህ አጋጣሚ የወያኔ መንግስት የአቶ ገብረ መድህንን ባለቤታቸውን ነፍሰጡር ሴት እንደገደለባቸው መግለጹ ተገቢ ነው። ኢሕአፓም የትግራይ ሪፑብሊክ ምስረታ የሚመለከተውን ሰነድ አባዝቶ ለመጀመሪያ ግዜ ለሕዝብ ይፋ አድርጓል። ኢሕአፓ ሕወሓት ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅት መሆኑን በግልጽ አሰቀምጧል።ኢሕአፓን ለሶስት ሕወሓት፣ ሻዕቢያና የሱዳን መንግስት ሆነው በ 1983 ዓ.ም. በመውጋት አጥፍተውታል።ሱዳን የነበሩት ቢሮዎቹ እንዲዜጉ ሲደረግ የተወሰኑ አባላቱ በወያኔ ታፍነው በሱዳን መንግስት ተባባሪነት ወደ ኢትዮጵያ ተወስደዋል።የኢሕአፓን አመራርን በቁጥጥር ስር ካደረገ በኋላ ወያኔ ረሽኗቸዋል።ምዕራባያውያንም ተባብረዋቸዋል።

3. የኢትዮጵያ ሕዝብ ናዚ ነው? „ትግሬ ወርቅ ነው፣ ከዚህ ዘር በመወለዴ እኮራለሁ" ያለው ጸረ-ኢትዮጵያ የባንዳው ልጅ መለስ ዜናዊ ነው። የብዙ ንጹሃን ዜጎች ደም በእጁ ላይ ያለና በትግሉ ዘመን ክውጊያ ሸሽቶ መገደል ሲገባው ተርፎ ስልጣን ላይ በመውጣት፣ ከሕግ በላይ ሆኖ የንጹሃን ዜጎችን ሕይወት ሲያስጨርስ ቆይቶ በኋላ ጭጭ እንዲል የተደረገ ጨካኝ ነው።ይህ አባባሉ ዘረኝነትና ምርጥ ነኝ ለማለት የዳዳበት ነው።ይኼ ደግሞ የጀርመኑን ሰውየ መንገድ መከተል ነው። ሌላው ነፍሰ ገዳይ ስዩም መስፍን ሰሞኑን በህወሓት መዝገበ ቃላት „የህወሓት የግፍ አገዛዝ ይብቃ" ብሎ ሕዝቡ ሲነሳ ለስዩም „ናዚነት" ከሆነ፣ በወያኔ ግፎች የሚሰቃየው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ „ናዚ" ነው ማለት ነው? ይሄ የሚያመራው በአማራው ክልል በተካሄደው ህዝባዊ አመጽ ንጹሃን የትግራይ ተወላጅ ላይ በአማራው አማካይነት እንደተካሄደ አድርጎ፣ የተለመደውን የወያኔ የእውሸት ፕሮፕጋንዳ ለማካሄድ ዓላማ ያደረገ ነው።ለዚህም የወያኔ መንግስት በአማራ ክልል ከነበሩት ውስጥ የተወሰኑትን የትግራይ ተወላጅ በአውሮፕላን ጭኖ ወደ ትግራይ መወሰዱ ይታወቃል።

ይህም ለወያኔ የዘር ፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ማካሄጃ ለማመቻቸት እንጂ በአማራው ክልል የሚኖሩ ንጹሃን የትግራይ ተወላጆች

ላይ የጥቃት እርምጃ አልተወሰደም።በወያኔ ሆዳሞች ላይ ግን እርምጃ መውሰዱ ግድ ነው። ምክንያቱም የወንጀሎቹና ግፎቹ ምንጮች ናቸውና። በዚህ አሳቦ ወደ ትግራይ ሕዝብ ያው የለመደውን ጸረ አማራ ፕሮፖጋንዳ ከዚህ በፊት ሕጻናትን „አማራው ሊበላህ ነው“ የሚለውን ዓይነት ለትግራይ ሕዝብ ለማስተጋባት የሚደረግ ከእወነት የራቀ ቅስቀሳ ነው።

4.የወያኔው ስዩም መስፍን ስለ ኢሕአፓና መኢሶን መጋበዝ፣ የወያኔው ስዩም መስፍን ሰሞኑን በሰጠው ቃለ መጠይቅ የትግራይን ሕዝብ እንደ ይሁዳዊ በማድረግ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግራይ ሕዝብ ላይ ጭፍጨፋ ለማካሄድ እንደተዘጋጀ በማስመሰል የከዚህ በፊቱን „የአማራ ሊበላህ ነው“ የትግራይ ልጆች ማስፈራሪያ እንደገና እንደ ፕሮፖጋንዳ ለመጠቀም እየወተወተ ነው። ለዚህም ኢሕአፓና መኤሶን ለ 25 ዓመት እየሰሩ እንደሆነ በመጥቀስ ካናዳ ላይ ተሰብስበው በሰጡት መግለጫዎች ሕወሓት የትግሬ የበላይነትን ሊያመጣ የሚፈልግ ፋሽስታዊ ድርጅትና ከደርግ በላይ ግፈኛ እንደሆነና የሚመሰረተውን የሽግግር መንግስት አንቀበልም በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዳይቀበል ጥሪ እንዳደረጉ የወያኔው ስዩም መስፍን በደንብ አድርጎ ዋሽቷል። ምክንያቱም ኢሕአፓም ሆነ መኢሶን በካናዳ በዚያን ወቅት ከሌሎች ድርጀቶች ጋር በመሆን አንድ የተቃዋሚ የጋራ የሆነ ድርጀት ለማቋቋም ቶሮንቶ ውስጥ ስብሰባ አድርገዋል።በዚህ ስብሰባም ሕወሓትና ሻዕቢያ እንዲሁም ሁሉም ሌሎች ድርጅቶች በስብሰባው እንዲገኙ ተጋብዘዋል።

ህወሓትና ሻዕቢያ በስብሰባው አልተገኙም ነበር።መግለጫም ወያኔን በሚመለከት ስብሰባውን ባደረጉበት ወቅት አላወጡም ነበር። የዚህ ስብሰባ ሌላ ቀጣይ ስብሰባ በኋላ አሜሪካ ውስጥ በሜርላንድ ተደርጎ ቅንጅት በመባል የሚታወቀው ድርጅት ተፈጥሯል። ወያኔ አዲስ አበባ በአሚሪካኖች ትብብር ገብቶ ከተቆጣጠረ በኋላ አንድ ቻርተር የወያኔ መንግስት አውጥቶ ነበር። በዚህ ቻርተር መሰረት ግዜያዊ የሽግግር መንግስት ለመመስረት በተደረገው ስብሰባ ላይ ኢሕአፓና መኢሶን እንዲሳተፉ ተጋብዘው አልፈልግም እንዳሉ የውያኔው ስዩም መስፍን ተናግሯል። ይህም እውሸት ነው። ምክንያቱም ህወሓት ከኢሕአፓ ጋር ጎጃም ውስጥ ጦርነት ግንቦትና ሚያዝያ 1983 ዓ.ም. በማካሄድ እንደነበርና ይህም በኢሕአዴግ ሕወሓት ሚያዝያ 10 ቀን 1983 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ „ሚያዝያ 8 ቀን 1983 ዓ.ም. በወሰደው የማጥቃት እርምጃ 74 የኢሕአፓ አባላትን ሲማርክ፣ 134 የሚሆኑ አባላቱን እንደገደለና እንዳቆሰለ“ ገልጿል።

የወያኔ ሰዎች ገድለውህ ለቅሶ ተቀምጠው የሚያስተዛዝኑ ግፈኞች መሆናቸው ይታወቃል።

ሌላው መኢሶን በ„ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ፣ መጋቢት/ሚያዝያ 1983 ፣7 ኛ ዓመት ቁጥር 10፣“ እትም ላይ ባወጣው „ኢሕአዴግ በድርጅቶች ላይ ስለሚያካሂደው ጦርነት ከመኢሶን የተሰጠ መግለጫ“ በሚለው ስር የሚከተለውን ጥሪ ለወያኔ መንግስት በወቅቱ አውጥቶ ነበር። „መኢሶን በተደጋጋሚ እንዳሳወቀው፣ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ አንድ ድርጅት ብቻ አዲስ አበባ ላይ ስልጣን ጨብጦ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁለ-ገብ ሰላምን ሊያስገኝና የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊ ሽግግርን ሊያረጋግጥ የሚችልበት ሁኔታ የለም።የዚህን ተቃራኒ የሚያምን ማንኛውም ድርጅት ሌሎች ድርጅቶችን በመሳሪያ ሃይል ደምስሶ ለማጥፋት ከመሻትና የጭቆና አገዛዙን ለማስፈን ከማቀንቀን በስተቀር፣ ከቶም የሰላምንና የዲሞክራስን ጎዳና ለመከተል የሚችል አይሆንም።

ኢሕአዴግ ይህንኑ አስተውሎና „እንወያይ“ በማለት በተደጋጋሚ የቀረበለትን ግብዣ ተቀብሎ ለውይይት እንዲቀርብ መኢሶን ጥሪውን ያድሳል።“ የሚል ነው። የወያኔው ስዩም መስፍን ኢሕአፓንና መኢሶንን የደርግ ስርዓት ስለፈረሰባቸው ወያኔን አምርረው እንደሚታገሉ ያው የተለመደውን እውሸት በትኗል። ሁለቱም ድርጅቶች ደርግን ለመጣል እንዳቅማቸው ታግለዋል። የእነርሱ ስጋት ደርግን ተክቶ ስልጣን ላይ የወጣው የወያኔ ዘረኛ መንግስት በመሆኑና ከወያኔ መንግስት ጠባብነትን፣ ዘረኝነትና ትምክህተኛነትን ካልሆነ በስተቀር፣ የሕዝብ ነጻነትና ዴሞክራሲያዊ አሰራር እውን የሚሆንበት ሁኔታ እንደማይፈጠር ነው።

5.ወልቃይት፣ ጠገዴና ራስ ዳሸን የትግራይ አስተዳደር ውስጥ እውን ነበሩ? የወያኔ ዘረኛና ተንኮለኞች ህቅን መሰረት ባላደረገ መልኩ የወልቃይትን ሕዝብ በተለያዩ መንገዶች በማጥቃት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳያሳዉቁ የትግራይን ክልል ለም መሬቶችን አጭበርብሮ በማግበስበስ ስፋቱን ለመጨመርና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኑ ጋር የትግራይን ሕዝብ ለማናከስ እስካሁኗ ደቂቃ እየተሟሟቱ ይገኛሉ። ለዚህም እውነቱን ለማወቅ የታሪክ ሰነዶችን ማገላበጡ ተገቢ ይሆናል። የወያኔ ዘረኞችንና ተንኮሎኞችን ሃሳብ ለመቀየር ሳይሆን፣ የትግራይና የተቀረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እውነቱን አውቆ ወጊዱ እንዲላቸው ለማስቻል የሚከተሉትን እወነታዎች ለማስጨበጥ ነው።

5.1.በአጼ ዮሓንስ ዘመን፣ አጼ ዮሐንስ ከ 1871 ዓ.ም. እስከ 1889 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ድረስ ኢትዮጵያን የመሩ ንጉስ ናቸው። “በአጼ ዮሐንስ ዘመን ወልቃይትና ጠገዴ በትግራይ ስር ስለነበሩ ነው አሁን ወደ ትግራይ የጠቀለልናቸው“ የሚለው የወያኔ አባባል እውሸት ነው።ምክንያቱም በአጼ ዮሐንስ ዘመን ወልቃይት፣ ጠለምት፣ ዋልድባ፣ አላማጣ፣ በሙሉ በትግራይ ስር አልነበሩም።በጎንደር ስር ነበሩ። በ 1880 ዓ.ም. The Earth and its Inhabitants“ በሚባለው በፈረንሳዩ የጂኦግራፊ

ፕሮፌሰር ኤሊሲ ሬክለስ በተጻፈው መጽሐፍ ክፍል አራት ገጽ 443 ላይ የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል።“The Amhara government provinces are: Dembia, Chelga, Yantangera, Daagossa, Kurrara, Begemdier, Guna, Saint, Wadla, Delanta, Woggera, Simen, Tselemt, Armachiho, Tsegede, Kolla Wogerra, Waldiba and Wolkait.“ በሚል ቁልጭ አድርጎ በአማራ መንግስት ስር የነበሩትን ግዛቶች አስቀምጧል።የወያኔ ተንኮልኞችና ዋሾዎች መሬት ስንጥቅ ብላ ትዋጣቸው። 5.2.በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን! የአጼ ቴዎድሮስ ዘመን ከ 1818 ዓ.ም. እስከ 1868 ዓ.ም. እ.ኤ.አ። ኢትዮጵያን የመሩ ንጉስ ናቸው። በእንግሊዛዊቷ ንግስት ትእዛዝ ስለኢትዮጵያ ከ 15 ኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን በአውሮፓውያን የተጻፉ መጻህፍት ተሰብስበው እንዲጠረዙና ለ“House of Common lower House“ ጥቅም ይውል ዘንድ በ 1867 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. እንደ አንድ መጽሐፍ እንዲታተም ተደርጓል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥም ስለ ወልቃይትና ጠገዴ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን ይሁን ከሳቸው በፊት በማን ስር ይተዳደሩ እንድነበር በዝርዝር ይገልጻል።

የመጽሐፉ ስም “Routes in Abyssinia“ (printed in 1867 G.C.)page 188 በሚል ነው።በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለው ቀርቧል። “The provinces of Amhara are: Simen, Waldibba, Wolkait, Wogera, Chilga, Kuara, Belesa, Fogerra, Damot, Gojjam, Begemidir, Beshilo.. .. .. .. .. Waldiba situated to the NW of Semein between the Tekeze and the Angereb, extends as far as the junction of the two rivers. Welkait is to the west of the Waldiba, it is intersected through its whole length by the two river tekuar and guang. It is more wooded than Waldiba.” Page 188 የትግራይ ክፍለ ሀገር ድንበርና ግዛት እንደሚከተለው ተገልጿል። “The territory of Tigray whose capital is Adwa is bounded on the west by Shire, on the south west by Temben and Adet on the south by Geralta, on the south East by Haramat, on the East by Agamae, and on the Nothr by the Rivers Mereb and Belessa.” Page 187-188 ዋና ከተማው አድዋ የሆነው የትግራይ ድንበር በምዕራብ ሽሬ፣ በደቡብ ምዕራብ ተምቤንና እደት፣ በደቡብ ጅራልታ(ጌራልታ)፣ በደቡብ ምስራቅ ሃራማት፣ በምስራቅ አጋሜ፣ በሰሜን መረብና በለሳ ወንዞች የሚያጠቃልል ነው።

5.3.በዘመነ መሳፍንት! ከአጼ ኢዮአስ ሞት ጀምሮ አጼ ቴዎድሮስ እስከሚነሱ ድረሰ የነበረው ግዜ ዘመነ መሳፍንት ሲባል፣ በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት አልነበራትም። በዚህ ማዕከላዊ አስተዳደር ባልነበረበት ዘመን እንኳን ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ዋልድባ፣ አላማጣ፣ ኮረምና የመሳሰሉ ቦታዎች በትግራይ ስር አልነበሩም። ጀምስ ብሩስ የተባሉ የስኮትላንድ ዜጋ ኢትዮጵያ መጥቶ በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ ምን ትመስል እንደነበረ በሰፊው አቅርቦታል። ስለ ትግራይ ግዛት “Travel to discover source of the Nile, Volume 3, Page 582” “Tigre is bounded by the territory of the Bahirenegash that is by the river Mereb on the East and Taccazze upon the west. It is about one hundred and twenty miles broad from E. to W. and two hundred from N. to S.” በማለት አስቀምጧል። Chapter 10 ላይ በመጽሐፉ ውስጥ ደግሞ “The first division is called Tigre, between Red Sea and the river Tekeze.Behneen that River(Tekeze) and the Nile Westwards where it bounds the Oromo, it is called Amhara.” ሲል ያብራራል። በተጨማሪም “Tekezze is the natural boundary between Tigre and Amhara” ሲል ገልጾታል።

5.4.በኢማኑኤል በሬዳ 1634 ዓ.ም. በኢማኑኤል በሬዳ በ 1634 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የተጻፈው መጽሐፍ በወቅቱ የነበረውን የትግራይን ግዛት በዝርዝር ሲያስቀምጥ፣ የትግራይ ድንበር ተከዜ እንጂ ተከዜን ተሻግረው ያሉትን ወልቃይትንና ጠገዴ ናቸው አላለም። የመጽሐፉ ስም “Tractatus tres historic – geographici(1634): A seventeenth century historical and geographical account of Tigray, Ethiopia(Aethiopistische Forschungen) 1634” የሚል ነው። 5.5.በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን! አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በ 14 ኛው ክፍለ ዘመን የነገሱ ንጉስ ናቸው። በ 37 ዓመታቸው የነገሱና የጥበብ ፍቅር ያላቸው እንደነበሩ ይነገርላቸዋል።በዘመናቸው ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል። ከነዚህም አንዱ በአክሱም ንቡረ ዕድ የተጻፈው “ዜና አክሱም መጽሐፍ” አንዱ ነው።በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ወሰንና ታሪክ ብቻ ሳይሆን፣ የክፍለ ሀገራቱንም ድንበር በደንብ መዝግቦታል።የትግራይንም ክልል በካርታና በጽሑፍ “Zena Axum Book” አስቀምጦታል።ይህም ወልቃይትና ጠገዴ በፍጹም የትግራይ ክልል እንዳልነበሩ የሚያሳይ ነው።ይህም “The Book of Axum.. shows a traditional schematic map of Tigray with its city Axum at its Center Surrounded by the thirteen principal provinces: Tembein, Shire, Seray Hamasen, Bur,Sama, Agame, Amba

Senait, Geralta, Enderta, Sahart and Abergele” የሚል ነው። ማጠቃለያ የወያኔ መንግስት ግፈኝነት፣ ዘረኝነት፣ ጠባብነት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አየፈጀ ያለበትና፣ በተመሳሳይ ከዚህ በፊት እንደለመደው የእውሸት ፕሮፓጋንዳ ወይም ቅስቀሳ የትግራይን ሕዝብ በመጠቀም በማካሄድ ያለበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

ውሸትን ዛሬም የወያኔ ባለስልጣናት እንደ እንድ የትግል ዘዴ በመጠቀም አየዋሹ በመቀስቀስ ላይ እንዳሉ ነው።ይህንን በተለይ የትግራይ ሕዝብ ሃቁን በመከታተል የወያኔ ባለስልጣናት የእውሸት ቅስቀሳ ሰላባ ላለመሆን ድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። በአገራችን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዜህ የወያኔ የዘር ፖለቲካ ለማላቀቅና ሁሉም ዜጋ በእኩልነት የሚኖርባትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የምትመሰረትበትን፣ እንዲሁም የመገንጠል ጥያቄ የማይነሳባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ሁለት አማራጮች ይኖራሉ። አንደኛው አማራጭ፣ በአገርና በሕዝብ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ሲባል የወያኔ መንግስት እንደ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በሚፈጠረው የሽግግር መንግስት ሲጠቃለልና ሲቋቋም ነው።

ይህም የወያኔ መንግስት የዴሞክራሲያዊ አሰራር መርሆችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሲቀበልና አሁን እንደ መንግስት የሚቆጣጠራቸውን የመንግስት መዋቅሮችን የስልጣን አውታሮች መሉ በሙሉ ራሱን ካገለለ፣ የመጨቆኛ መሳሪያዎቹ ፈርሰው ስልጣኑን ለሚቋቋመው የሽግግር መንግስት የሚያስረክብ ሲሆን ብቻ ነው። ሁለተኛው አማራጭ፣ የወያኔ መንግስት በአንደኛው አማራጭ መሰረት ሰላማዊ ሽግግሩን የማይቀበል ከሆነ፣ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች በሙሉ የጋራ የሽግግር መንግስት ፕሮግራም በጋራ ነድፈው፣ ለነደፉትና ለተስማሙበት የሽግግር መንግስት ፕሮግራም ትግላቸውን መቀጠል ይሆናል። የመጀመሪያው ዓላማቸው የዘረኛውን የወያኔ መንግስት ከስልጣን ማስወገድና ከዚያ የጋራ የሽግግር መንግስት ለማቋቋምና ፕሮግራሙን ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል።

ተንሳይት በቃና
ሰፕቴምበር 19 ቀን 2016 ዓ.ም.

http://www.ethiopanorama.com